DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF EDUCATION

OSSE

በልግ 2015

የተከበሩ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በዲሲ ግዛት የትምህርት ጉዳይ ዋና ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንቴንደንት ቢሮ በግዛቱ ውስጥ በሚገኙት ሁሉም ትምህርት ቤቶች በ2015-2016 ዓ.ም የክረምት የዝግ ወቅት ከመንግስት እና የመንግስት ቻርተርድ ትምህርት ቤቶች ጋር በትምረት በመሆን በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለአደጋ ያላቸዉን የተጋላጭነት ባህሪ ለማጥናት የሚያስችል ዳሰሳዊ ጥናት ያካሂዳል:: **ልጅዎት በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ ተሳትፎ እንዳያደርግ የሚፈልጉ ከሆነ የዚህን ደብዳቤ የመጨሻ ክፍል በመሞላት ወደ ትምህርት ቤቱ ይመልሱት::**

የወጣቶች የአደጋ ተጋላጭነት ባህሪ ዳሰሳዊ ጥናቱ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የሚገኙ ታዳጊዎች እና አዋቂዎች ለሞት አደጋ፣ ለአካል ጉዳት እንዲሁም ለማህበራዊ ቀዉሶች የሚያጋልጡዋቸዉን ባህሪያት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ዳሰሳዊ ጥናት ነዉ:: ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ለጤና አደጋ የሚያጋልጡ ባህሪያት ያልታሰበባቸዉ አደጋዎች እንዲሁም ጥቃቶች፣ ወሲባዊ ባህሪያት፣ አልኮሆል እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን መጠቀም፣ ሲጋራ ማጨስ፣አግባብ ያልሆነ አመጋገብ፣ እንዲሁም በቂ ያልሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ናቸዉ:: የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በዋነኝነት በሁለት የጤና ጠንቆች ዙሪያ መረጃን ያሰባስባል፣ እነሱም ከልክ ያለፈ ዉፍረት(ኦቤሲቲ) እና አስማ ናቸዉ:: ሪፖርት የሚደረጉትን ዳታዎች በማሰባበስ በአሜሪካ የሚገኙ ወጣቶች ያላቸዉን ወሲባዊ ባህሪያት ለአካባቢዉ ማህበረሰብ፣ ለሀገራዊ ትኩረት፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ ለአለም አቀፍ የትኩረት አቅጣጫነት ጥቅም ላይ የሚያዉለዉ ሲሆን በመታየት ላይ ያሉ አዝማሚያዎችን ለመመርመር እንዲሁም በጊዜ ሂደት የታዩ ለዉጦችን ለመገምገም ጥቅም ላይ ይዉላል:: ተጨማሪ መረጃዎችን ቀጥሎ ከተመለከተዉ ድረ-ገጽ ማግኘት ይችላሉ:
http://www.cdc.gov/HealthyYouth/yrbs/index.htm

ይህ ዳሰሳዊ ጥናት በመጠይቅ ፎርማት የተዘጋጀ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች በአንድ ክፍለ ጊዜ ማለትም በ45 ደቂቃ ውስጥ የሚሞሉት መጠይቅ ነዉ:: በመጠይቁ ላይ የተማሪዎች ማንነት ተለይቶ የማይገለጽ ስለሆነ ተማሪዎች ነጻ ሆነዉ ለሁሉም ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ እንዲሰጡ አጋጣሚዉን ይፈጥርላቸዋል:: ይህ ዳሰሳዊ ጥናት በተማሪዎች መልካም ፈቃድ የሚከናወን እንደመሆኑ ተማሪዎች መጠይቁን ባለመሙላታቸዉ ምክኒያት የሚደርስባቸዉ ቅጣት አይኖርም፣ ሆኖም ጥናቱ አስፈላጊ በመሆኑ ምክኒያት የተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እጅግ ይበረታታል::

**ልጅዎት በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ የሚሳተፍ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ድርጊት አይጠበቅበትም::** ሆኖም ልጅዎት በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ እንዲሳተፍ የማይፈልጉ ከሆኑ ከታች የተመለከተዉን ክፍል በሙላት፣ ከፈረሙ በኋላ ልጅዎት ወደ ሚማርበት ትምህርት ቤት በመሄድ ከኦክቶበት 1፣2015 ዓ.ም በፊት ባለዉ ጊዜ ውስጥ ያስገቡ:: ጥያቄ ካልዎች እባክዎን የልጅዎትን መምህራን ወይም ርእሰ መምህራንን በማነጋገር ምላሽ ያግኙ:: በተጨማሪም ሚ/ር ካፉኢ ዶኢ በዚህ ስልክ ያነጋግሩ 202-741-6484 ወይም በዚህ የኢሜይል አድራሻ ይተቀሙ osse.hydt@dc.gov.

ከሰላምታ ጋር፣

Unique Morris-Hughes, Ph.D.
Chief Operating Officer
Office of the Chief Operating Officer (COO)

**የተማሪው ስም:** ______________________________

ትምህርት ቤት: ______________________________ ክፍል: ____________

ይህንን ቅጽ አንብቤ ስለ ምን ጉዳይ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ::

**[ ] አያይ፣ ልጄ በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ላይ ባይሳተፍ እመርጣለሁ::**

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ: ______________________ቀን: ____________